# መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡

# ሦስቱ ፡

ንባብ ፡ ከነትርጓሜ ።

ከሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪ ፡ ተተረጐመ ።

ግርማዊ፡ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ፡ በሃያ፡ ስምንተኛው ፡ዘመነ፡ መንግሥት ።
ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሆኑ ፡ በ፱ኛው ፡ ዓመት ፡

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤ ቍ ፡ 1608

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ ።

## የሐዋርያት፡ሥራ ።


| አርእስት ። | ምዕራፍ ። | ቁጥር፡ | ገጽ፡ |
|---|---|---|---|
| ስለ፡ጌታችን፡ዕርገት፡ | ፩ | ፪ | ፲፫ |
| ከሐዋርያት፡ጋራ፡ስለ፡መብላቱ፡ | » | ፬ | ፲፮ |
| ስለ፡ይሁዳ፡ | » | ፲፮ | ፲፱ |
| ስለ፡ማትያስ፡ | » | ፳፫ | |
| ስለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ | ፪ | ፩ | ፳፪ |
| ስለ፡ኢዩኤል፡ትንቢት፡ | » | ፲፮ | ፳፮ |
| ስለ፡ጴጥሮስና፡ዮሐንስ፡ወደ፡ምኵራብ፡መግባት፡ | ፫ | ፩ | ፴፫ |
| ስለ፡ጴጥሮስና፡ዮሐንስ፡ሕዝቡን፡ማስተማር፡ | ፬ | ፩ | ፴፯ |
| ትንቢት፡ስለ፡ክርስቶስ፡ | » | ፳፭ | ፵ |
| ስለ፡ሐናንያና፡ስለ፡ምሽቱ፡መሐላ፡ማፍረስ፡ | ፭ | ፩ | ፵፫ |
| ስለ፡ቴዎዳስ፡ | » | ፴፮ | ፵፯ |
| ስለ፡ይሁዳ፡ዘገሊላ፡ | » | ፴፯ | » |
| ስለ፡እስጢፋኖስ፡ሹመት፡ | ፮ | ፫ | ፶ |
| ስለ፡አብርሃም፡ጥሪ፡ | ፯ | ፪ | ፶፫ |
| ስለ፡ዮሴፍ፡መሸጥ፡ | » | ፱ | ፶፯ |
| ስለ፡ሙሴ፡መወለድ፡ | » | ፳ | ፷፯ |
| ስለ፡ሙሴ፡ወደ፡ግብጽ፡መላክ፡ | » | ፴፬ | ፸፫ |
| ስለ፡ጣዖት፡ማቆም፡ | » | ፵ | ፸፭ |
| ስለ፡ደብተራ፡ኦሪት፡ | » | ፵፬ | ፸፮ |
| ስለ፡እስጢፋኖስ፡ሞት፡ | » | ፶፩-፷ | ፸፯-፸፱ |
| ስለ፡ምዕመናን፡መበተን፡ | ፰ | ፩ | ፸፱ |
| ስለ፡ፊልጶስ፡ማስተማር፡ | » | ፭ | ፹-፹፭ |
| ስለ፡ሲሞን፡ | » | ፱ | ፹፩ |
| ስለ፡ኢትዮጵያዊው፡ሹም፡ዕምነት፡ | » | ፳፮-፴፱ | ፹፫ |
| ስለ፡ጳውሎስ፡ሹመትና፡ዕምነት፡ | ፱ | ፩-፳፫ | ፹፭ |
| ስለ፡ኤንያ፡ድኅነት፡ | » | ፴፫-፴፭ | ፺ |
| ስለ፡ጣቢታ፡ትንሣኤ፡ | » | ፴፮-፵፩ | ፺፩ |
| ስለ፡ቆርኔሌዎስ፡ | ፲ | ፩-፵፮ | ፺፪ |
| ስለ፡ጴጥሮስ፡ራእይ፡ | ፲፩ | ፭ | ፺፱ |
| ስለ፡ያዕቆብ፡ሞትና፡ስለ፡ጴጥሮስ፡እሥራት፡ | ፲፪ | ፩-፳ | ፻፪ |
| ስለ፡ሄሮድስ፡ቀጥዓ፡ | » | [illegible] | [illegible] |





| አርእስት ። | ምዕራፍ ። | ቁጥር፡ | ገጽ፡ |
|---|---|---|---|
| ስለ፡በርያሱስና፡ስለ፡ሰርግዮስ፡ | ፲፫ | ፮-፲፫ | ፻፮ |
| ስለ፡ሳኦልና፡ስለ፡ዳዊት፡ | » | ፲፮-፳፫ | ፻፯ |
| ልምሾ፡ስለ፡ነበረው፡ድውይ፡ድኅነት፡ | ፲፬ | ፯ | ፻፲፫ |
| ለጳውሎስና፡ለበርናባስ፡መሥዋዕት፡ስለ፡ማቅረብ፡ | » | ፲፩ | » |
| ስለ፡ጳውሎስ፡በደንጊያ፡መወገር፡ | » | ፲፱ | ፻፲፮ |
| ስለ፡ያዕቆብ፡ትምህርት፡ | ፲፭ | ፲፫ | ፻፳፩ |
| ስለ፡ጳውሎስና፡ስለ፡በርናባስ፡መለያየት፡ | » | ፴፮-፵፩ | ፻፳፬ |
| ጋኔን፡ስላደረባት፡ብላቴና፡ | ፲፮ | ፲፯ | ፻፳፯ |
| ስለ፡ጳውሎስና፡ስለ፡ሲላስ፡መታሠር፡ | » | ፲፱ | ፻፳፰ |
| ወደ፡ቤርያ፡ሸሽቶ፡ስለ፡መሄድ፡ | ፲፯ | ፲ | ፻፵፪ |
| በአቴና፡ስለ፡ጳውሎስ፡ማዘን፡ | › | ፲፮ | » |
| በአርዮስ፡ፋጎስ፡ስለ፡ማስተማር፡ | » | ፲፱ | ፻፵፫ |
| ስለ፡አቂላና፡ስለ፡ጵርስቅላ፡ | ፲፰ | ፪ | ፻፵፯ |
| ስለ፡ጳውሎስ፡ራእይ፡ | » | ፱ | ፻፵፰ |
| ስለ፡አጵሎስ፡በቆሮንቶስ፡ማስተማር፡ | ፲፱ | ፩ | ፻፶፩ |
| በልብሱ፡ድውያንን፡ስለ፡ማዳን፡ | » | ፲፩ | ፻፶፫ |
| ስለ፡ደቂቀ፡አስቄዋ፡ | » | ፲፫ | » |
| ስለ፡ድሜጥርስና፡ስለ፡አርጤምስ፡ | » | ፳፬ | ፻፶፬ |
| ስለ፡ብላቴናው፡መውደቅ፡ | ፳ | ፱ | ፻፶፱ |
| ስለ፡ፊልጶስ፡ | ፳፩ | ፰ | ፻፷፭ |
| ስለ፡ጳውሎስ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡መውጣት፡ | » | ፲፭ | ፻፷፮ |
| በዓለ፡አንጽሖ፡ስለ፡ማድረግ፡ | » | ፳፮ | ፻፷፯ |
| ስለ፡ሰዱቃውያንና፡ስለ፡ፈሪሳውያን፡መለያየት፡ | ፳፫ | ፮ | ፻፸፬ |
| ሊቀ፡ካህናቱ፡ሐናንያ፡ወደ፡ቂሣርያ፡ስለ፡መሄድ፡ | ፳፬ | ፩ | ፻፸፱ |
| ስለ፡ፊልክስና፡ስለ፡ዱርሳሌም፡ | » | ፳፬ | ፻፹፪ |
| ስለ፡አግሪጳና፡ስለ፡በርንቄ፡ | ፳፭ | ፲፫ | ፻፹፭ |
| ጳውሎስ፡ወደ፡ቄሣር፡ስለ፡መላክ፡ | ፳፯ | ፩ | ፻፺፪ |
| ስለ፡ጳውሎስ፡ራእይ፡ | » | ፳፪-፳፭ | ፻፺፭ |
| ስለ፡ጳውሎስና፡ስለ፡ፑፕልዩስ፡ | ፳፰ | ፩-፲፩ | ፻፺፰ |
| ወደ፡ሮሜ፡ስለ፡መድረሱ፡ | » | ፲፬ | ፻፺ |
| ስለ፡ጳውሎስ፡በሮሜ፡ቦታ፡መግዛት፡ | » | ፴ | ፻፺፬ |


### ፩ኛ፡ጴጥሮስ፡


| | | | |
|---|---|---|---|
| በክብር፡ላይ፡መከራ፡በመከራ፡ላይ፡ክብር፡ | ፩ | ፫-፱ | ፪፻፱ |
| በሃይማኖት፡ፍጻሜ፡የነፍስ፡ድኅነት፡ | » | ፱ | ፪፻፲፬ |
| የነቢያት፡ፍላጎት፡ | » | ፲-፲፫ | » |



www.ethiopianorthodox.org

| አርእስት ። | ምዕራፍ ፡ | ቁጥር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|---|
| ሕፃናትን ፡ መምሰል ፡ | ፪ | ፩-፬ | ፪፻፳፪ |
| የሥጋን ፡ ፍትወት ፡ ማራቅ ፡ | » | ፲፩ | ፪፻፳፯ |
| ሴቶች ፡ ለባሎቻቸው ፡ መገዛት ፡ | ፫ | ፩ | ፪፻፴፫ |
| ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ መልስ ፡ ማዘጋጀት ፡ | » | ፲፫ | ፪፻፴፱ |
| የክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ መሞት ፡ | » | ፲፰-፳ | ፪፻፵፩ |
| መከራን ፡ አለመሰቀቅ ፡ | ፬ | ፲፪ | ፪፻፵፯ |
| መምህራንና ፡ ምዕመናን ፡ | ፭ | ፩-፲፩ | ፪፻፵፱ |

## ፪ኛ ፡ ጴጥሮስ ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| የምግባር ፡ ስልት ፡ | ፩ | ፭-፰ | ፪፻፶፭ |
| አብ ፡ ለልጁ ፡ ምስክር ፡ | » | ፲፯ | ፪፻፷ |
| ስለ ፡ ኖኅ ፡ | ፪ | ፭-፰ | ፪፻፷፬ |
| ስለ ፡ በለዓም ፡ | » | ፲፯ | ፪፻፷፯ |
| ምሳሌ ፡ ሰሎሞን ፡ | » | ፳፪ | ፪፻፸፩ |
| ነገረ ፡ ምጽአት ፡ | ፫ | ፩-፲፬ | » |

## ፩ኛ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| የቀድምናው ፡ ነገር ፡ | ፩ | ፩-፰ | ፪፻፸፰ |
| ስለዚህ ፡ ዓለም ፡ ከንቱነት ፡ | ፪ | ፲፭ | ፪፻፹፭ |
| ኃጢአት ፡ ከጋኔን ፡ | ፫ | ፯-፲፯ | ፪፻፺፩ |
| ፍቅር ፡ በእግዚአብሔር ፡ | ፬ | ፯-፳ | ፪፻፺፯ |
| በሃይማኖት ፡ ዓለምን ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ | ፭ | ፩-፳ | ፪፻፺፱ |

## ፪ኛ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| በዚህ ፡ ዓለም ፡ መናፍቃን ፡ | ፩ | ፯ | ፫፻፯ |
| መናፍቅን ፡ አለመቀበል ፡ | » | ፱ | » |

## ፫ኛ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስለ ፡ ዲዮጥራጥስ ፡ | ፩ | ፱ | ፫፻፲ |
| ስለ ፡ ድሜጥሮስ ፡ | » | ፲፪ | » |

## የያዕቆብ ፡ መልእክት ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስለ ፡ ትዕግሥት ፡ | ፩ | ፬ | ፫፻፲፫ |
| ስለ ፡ ባለጸጋና ፡ ስለ ፡ ድሀ ፡ | » | ፱ | ፫፻፲፬ |
| ፈጥኖ ፡ መስማት ፡ ከመናገር ፡ መዘግየት ፡ | » | ፲፱ | ፫፻፲፯ |
| የባለጸጋ ፡ ልጅና ፡ የድሀ ፡ ልጅ ፡ | ፪ | ፩-፭ | ፫፻፳ |
| ሃይማኖት ፡ ያለምግባር ፡ | » | ፲፬ | ፫፻፳፫ |
| ዘለፋ ፡ መምህራን ፡ | ፫ | [illegible] | [illegible] |

www.ethiopianorthodox.org



| አርእስት ። | ምዕራፍ ፡ | ቁጥር ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|---|
| ፀብ ፡ ክርክር ፡ | ፬ | ፩ | ፫፻፴ |
| ባለጸጎችና ፡ ድሆች ፡ | ፭ | ፩ | ፫፻፴፬ |
| ስለ ፡ ኢዮብ ፡ ትዕግሥት ፡ | » | ፲፩ | ፫፻፴፯ |
| ጸሎት ፡ ለድውይ ፡ | » | ፲፬ | ፫፻፴፯ |
| ጸሎት ፡ እንዲጠቅም ፡ | » | ፲፯-፳ | ፫፻፴፰ |

## የይሁዳ ፡ መልእክት ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ | ፩ | ፬ | ፫፻፵፩ |
| ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ስለሙሴ ፡ | » | ፱ | ፫፻፵፪ |
| የሄኖክ ፡ ትንቢት ፡ | » | ፲፬ | ፫፻፵፬ |

## ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስለ ፡ ምጽአት ፡ | ፩ | ፯ | ፫፻፶፰ |
| ሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ | » | ፲፩ | ፫፻፷ |
| በሰማይ ፡ መንበር ፡ | ፬ | ፪ | ፫፻፷፯ |
| የተጻፈች ፡ መጽሐፍ ፡ | ፭ | ፩ | ፫፻፸፩ |
| መጀመሪያው ፡ ቁልፍ ፡ | ፯ | ፩ | ፫፻፸፭ |
| አራት ፡ መላእክት ፡ በነፋስ ፡ | ፯ | ፩ | ፫፻፹፬ |
| ሰባት ፡ መላእክት ፡ | ፰ | ፪ | ፬፻ |
| የሰበድአት ፡ ታሪክ ፡ | ፱ | ፩ | ፬፻፬ |
| የእስክንድር ፡ ታሪክ ፡ | » | ፲፩ | ፬፻፯ |
| ሰባቱ ፡ ምስጢራት ፡ | ፲ | ፬ | ፬፻፲፯ |
| ሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ በአፍአ ፡ | ፲፩ | ፩ | ፬፻፲፰ |
| ራእይ ፡ በእንተ ፡ ብእሲት ፡ | ፲፪ | ፩ | ፬፻፳፫ |
| ሚካኤል ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ | » | ፯ | ፬፻፳፭ |
| ስለሐሣዌ ፡ መሢሕ ፡ አነሣስ ፡ | ፲፫ | ፩ | ፬፻፴ |
| ወልድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ | ፲፬ | ፩ | ፬፻፴፭ |
| የደቂቀ ፡ ኬሬቢ ፡ ታሪክ ፡ | ፲፯ | ፲፪ | ፬፻፵፯ |
| ሽሕ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ | ፳ | ፬ | ፬፻፶፭ |
| ዳግም ፡ ምጽአት ፡ | » | ፲፩ | ፬፻፶፯ |
| ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ | ፳፩ | ፲-፳፯ | ፬፻፷ |
| አምስት ፡ ውሾች ፡ | ፳፪ | ፲፭ | ፬፻፸፩ |

መግቢያ ።

፩ኛ ፤ ግብረ ፡ ሐዋርያት ።

፪ኛ ፤ ፺ቱ ፡ መልእክታተ ፡ ሐዋርያ ።

፫ኛ ፤ ራእየ ፡ ዮሐንስ ።

እሊህን ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡ ለ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ መብራቶች፡ መሆናቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አስፈቅደን ፡ እንዲታተሙ ፡ ስለፈቀዱልን ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ አዘጋጅተን ፡ አሳትመናል ።

ክሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪ ፡ ተተረጕመ ።

መጽሐፈ፡ ግብረ፡ ልኡካን፡ ዝ፡ ውእቱ ፡ ዜና፡ ሐዋርያት፡ ንጹሓን፡ እምጊዜ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወፈነዎ ፡ ኀበ ፡ ተዮፊላ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ወንጌለ ።

ይህ ፡ ቃል ፡ የሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ ነው ፡ ጥንተ ፡ ነገሩስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልብ ፡ የመከረውን ፡ በነቢያት ፡ ያናገረውን ፡ ለመፈጸም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡ ሥጋም ፡ ሆኖ ፡ሕገ ፡ ጠባይዐዊን ፡ ሕገ ፡ መጽሐፋዊን ፡ እየፈጸመ ፡ አደገ ፡ ሕገ ፡ ጠባይዐዊ ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግ ፡ ነው ፡ ዕንጨት ፡ እየሰበሩ ፡ ውኃ ፡ እየቀዱ ፡ እናት ፡ አባትን ፡ ማገልገል ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ልህቀ ፡ በበሕቅ ፡ እንዘ ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለአዝማዲሁ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እሙ ፡ እንዲል ፡ (ወለይእቲም ፡ ይላል) ፡ ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፶፩ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፋዊ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ መፈጸም ፡ ነው ፡ ሕገ ፡ ኦሪትንስ ፡ መፈጸም ፡ እንደ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እግዚአ ፡ ለኦሪት ፡ ገብረ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከመ ፡ ይሣየጠሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፡ ወገብረ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ እንዲል ፡ ገላት ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ በ፰ ፡ ቀን ፡ ቤተ ፡ ግዝረት ፡ ባ፹ ፡ ቀን ፡ እጕለ ፡ ርግብ ፡ ዘውገ ፡ ማዕነቅ ፡ ይዞ ፡ ለመባረክ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መግባት ፡ ካመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ለበዓል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መውጣት ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ለለዓመት ፡ ለበዓል ፡ ለያስተርኢ ፡ ተባዕትከ ፡ ወኵሉ ፡ ዘኢ.ዐርገ ፡ ለበዓል ፡ ርጉም ፡ ውእቱ ፡ እንድትል፡ ኦሪት ፡ ዘፀአ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯ ፡ በቀሩት ፡ ሌዋውያን ፡ ግን ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ እንዳይወጡ ፡ ሥርዐት ፡ ተሠርቶባቸዋል ፡ ጌታ ፡ ግን ፡ ባሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ወጥቷል ፡ መውጣቱም ፡ ለማስተማር ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለሌላ ፡ አይደለም ፡ እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ሲመላው ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተጠምቆ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነቱን ፡ ከአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ አስመስክሮ፡ ዕለቱን፡ ወደ፡ ገዳም፡ ሄደ፡ ማቴ፡ ፫፡ ፲፯። ማር፡ ፩፡፱። ሉቃ፡ ፳፩ ፡ በገዳም፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት፡ ጾመ፡ መዋዕለ፡ ጾሙ፡ ሲፈጸም ፡ ሰይጣን ፡ በሦስት ፡ ነገር፡ ተፈታተነው፡ በትዕቢት፡ በሥስት፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ በትዕቢት፡ ቢመጣበት፡ በትሕትና፡በሥስት ፡ ቢመጣበት ፡ በትዕግሥት፡ በፍቅረ፡ ንዋይ፡ ቢመጣበት፡ በጸሊአ ፡ ንዋይ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ሦስት ፡ አርእስት ፡ ኃጣውእ ፡ የሚባሉ፡ እሊህ፡ ናቸው፡ ዛሬም፡ ሰው፡ በእሊህ ፡ ድል፡ ከነሣ፡ የቀሩት፡ ኃጣውእ፡ አይቆሙለትም፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ምድረ፡ እስራኤል፡ ገብቶ፡ ትምህርቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ዠመረ፡ የቃሉን ፡ ትምህርት ፡ ሰምተው፡ የእጁን፡ ተአምራት ፡ አይተው ፡ ካሥር ፡ እህጉር፡ ከብዙ፡ መንደር ፡ ተወጣጥተው፡ አምስት ፡ ገባያ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ፡ ከእሊህም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹን ፡ ይመርጣል ፤ አስቀድሞ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ሐዋርያት ፡ ይመርጣል ፡ (ጥቅ) ፡ ወረሰየ ፡ እምሰብአ ፡ ዚአሁ ፡ ሐዋርያተ ፡ እንዲል ፡ ኤፌ ፡ ፬፡ ፲፩ ። ኋላም ፡ ፸፪ቱን፡ አርድእት ፡ ይመርጣል ፤ (ጥቅ)፡ ወኀረየ ፡ ካልአነ ፡ ሰብአ ፡ እንዲል ፡ ፸ም ፡ ይላል፡ ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ቀጥሎም ፡ ፴፮ቱን ፡ ቅዱ

www.ethiopianorthodox.org

ሳት ፡ አንስት ፡ ይመርጣል ፤ መቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ የሚባሉ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ ለዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ በእየዕፃቸው ፡ እየገባ ፡ ወር ፡ ወር ፡ ይሰብክላቸዋል ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ከዋለበት ፡ ይውላሉ ፡ ካደረበት ፡ ያድራሉ ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ አይከፈልባቸውም ፡ የቀሩትን ፡ ግን ፡ ምሽት ፡ ይከለክላቸው ፡ ነበር ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሮ ፡ ትምህርት ፡ በምር ፡ ሲረዳለት ፡ ለመድኃኒተ ፡ ዓለም ፡ በቀራንዮ ፡ ተሰቀለ ፡ (ጥቅ) ፡ ወገብረ ፡ መድኃኒተ ፡ በማዕከለ ፡ ምድር ፡ ኢይደልዎ ፡ ለነቢይ ፡ መዊት ፡ በአፍአ ፡ ዘእንበለ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንዲል ፡ መዝ ፡ ፸፬ ፡ ፲፪ ። ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፴፫ ።

ተሰቅሎም ፡ በሞቱ ፡ ዓለምን ፡ አድኖ ፡ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፡ ተነሣ ፡ (ጥቅ) ፡ በሰኑይ ፡ ዕለት ፡ ይቀሥፈነ ፡ ወበሰሉስ ፡ መዋዕል፡ ይሤርየነ፡ ወያሐይወነ፡ ወአመ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ንትንሣእ ፡ ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፪ ። ወአመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሦጣ ፡ ለነፍሱ ፡ ውስተ፡ ሥጋሁ ፡ እንዲል ፡ (አፈ፡ ወርቅ ፡ ቅዳሴ)፡ ተነሥቶም ፡ ለሐዋርያት ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ መጽሐፈ፡ ኪዳንን፡ ሲያስተምራቸው፡ ሰነበተ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጉባኤ ፡ ሠርቶ ፡ የትንሣኤ ፡ የአግብኦተ ፡ ግብር ፡ የጥብርያዶስ ፡ (ጥቅ) ፡ ወዝንቱ ፡ ሣልሱ ፡ እንዘ ፡ ያስተርእዮሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥአ ፡ እሙታን ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፲፬ ። በበዛው ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ (የጉባኤውን) ፡ በቀረው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ለአንዱም ፡ ለሁለቱም ፡ ባለሚሎቹ ፡ ሳይታያቸው ፡ አይውልም ፡ አያድርም ፡ ነበረ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በተነሣ ፡ ባርባ ፡ ቀን ፡ አንትሙሰ ፡ ንበሩ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኃይለ ፡ እምዓርያም፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ነግሯቸው ፡ ትእዛዙን ፡ አዝዞአቸው ፡ ዐረገ ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፱ ፡ ፶፩ ። ባረገ ፡ ባሥረኛው ፡ ቀን ፡ በተነሣ ፡ በአምሳኛው ፡ ቀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ላከላቸው ፡ እስከዚያ ፡ ወዴት ፡ ኖሮ ፡ ቢሉ ፡ በዘጠኙ ፡ ከተማ ፡ ካሉ ፡ መላእክት ፡ ሥጋዌውን ፡ ያላወቁ ፡ ነበሩና ፡ ለእነዚያ ፡ ሲያስተምር ፡ ሰንብቶ ፡ ይህማ ፡ ፈጣሪ ፡ ፍጡር ፡ ይመስል ፡ አንዱን ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ አንዱ ፡ ሥራ ፡ ይከፈልበታልን ፡ ብሎ ፡ ባሥረኛው ፡ ቦታ ፡ የገባን ፡ እኛ ፡ ነበርንና ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ቦታችን ፡ እንደ ፡ መለሰን ፡ ለማጠየቅ ። አንድም ፡ እኔ ፡ ዐሥሩን ፡ ቃላት ፡ ፈጽሜ ፡ ዐሥሩን ፡ ሕዋሳት ፡ ፈጥሬ ፡ እንደ ፡ ሰጠኋችሁ ፡ እናንተም ፡ ዐሥሩን ፡ ቃላት ፡ ዐሥሩን ፡ ሕዋሳት ፡ ብትጠብቁ ፡ ይሰጣችኋል ፡ ለማለት ፡ ሐዋርያትም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡ ፍሩሀን ፡ የነበሩ ፡ ጥቡዓን ፡ ሆኑ ፡ ከብልየት ፡ ታደሱ ፡ በአእምሮ ፡ ጎለመሱ ፡ ምሥጢር ፡ ተረጐሙ ፡ ባንድ ፡ በእብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፡ ሰባ ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ ተጨመረላቸው ፡ መዲናቸው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ዓመት ፡ በኅብረት ፡ አስተማሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሑሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ያላቸውን ፡ ያውቃሉና ፡

ይህን ፡ ዓለም ፡ ዕፃ ፡ በዕፃ ፡ ብለው ፡ ተካፍለው ፡ ለማስተማር ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ምድረ ፡ ዕርዕ ፡ ደርሳዋለች ፡ ለሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ዕፃ ፡ የላቸው



ም ። አንዱም ፡ ሁለቱም ፡ አንዱን ፡ ሐዋርያ ፡ እየተከተሉ ፡ ይሄዳሉ ፡ ሉቃስም ፡ ዮሐንስን ፡ ተከትሎ ፡ ሂዷል ፡ ከሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ከፍሎ ፡ መቄዶንያ ፡ የምትባል ፡ ሀገር ፡ አስተምር ፡ ብሎ ፡ ሰጥቶታል ። ከዚያ ፡ ገብቶ ፡ ጌታ ፡ ከፅንስ ፡ ዠምሮ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ቢነግራቸው ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ አመኑ፡ተጠመቁ ፡ ትምህርት ፡ ካልደረሰበት ፡ ለማዳረስ ፡ በሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ተዖፊላ ፡ መኰንነ ፡ እስክንድር ፡ ይለዋል ፡ ይህች ፡ እስክንድር ፡ በባጠገብ ፡ ያለች ፡ ሀገር ፡ ናት ፡ በሱ ፡ ስብከት ፡ አምኗል ፡ (አምናለች) ፡ ዜና ፡ ሐዋርያትን ፡ ጻፍልኝ ፡ ብሎት ፡ ጽፎለታል ፡ አጻጻፉም ፡ አምስት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ እንዳረገ ፡ መቶ ፡ ኻያው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ባንድነት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ። ይሁዳ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ በይሁዳ ፡ እግር ፡ ማትያስ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ባንድነት ፡ ሳሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ወረደላቸው ፡ በኢየሩሳሌም፡ የነበሩ፡ አይሁድ ፡ እስጢፋኖስን፡ በደንጊያ፡ ወግረው ፡ እንደ ፡ ገደሉት ፡ ይልቁንም ፡ መምህሩ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከእምነት ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞት ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ጻፍልኝ ፡ ብሎት ፡ ጽፎለታል ፡ መጻፉም ፡ ይኸ ፡ ባለው ፡ ብንጸና ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ ብልት ፡ ማኅበር ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ልንሆንበት ፡ ልንመከርበት ፡ ልንገሠጽበት ፡ (ጥቅ) ፡ ወኵሉ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለተግሣጸ ፡ ዚአነ ፡ ተጽሕፈ ፡ ከመ ፡ በትእግሥትነ ፡ ወበተወክሎ ፡ መጻሕፍት ፡ ንርከብ ፡ ተስፋነ ፡ እንዲል ። አርእስት ፡ የሰጡ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ናቸው ።

በዘመናቸው ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ መክስምያኖስ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ዓላውያን ፡ ነገሥታት ፡ ተነሥተው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይትዐጸዋ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ይትረኃዋ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተተኰሱ ፡ መጻሕፍት ፡ ፈለሱ ፡ ከምእመናንም ፡ ወገን ፡ የሚሞቱት ፡ ሞቱ ፡ የሚሰደዱትም ፡ ተሰደዱ ፡ ዘመኑም ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ከመከራውም ፡ ጽንዓት ፡ የተነሣ ፡ ዘመነ ፡ ሰማዕታት ፡ ተብሏል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተባርዮ ፡ የማያስቀር ፡ እግዚአብሔር ፡ ራትዕ ፡ ንጉሥ ፡ መፍቀሬ ፡ ሃይማኖት ፡ ቈስጠንጢኖስን ፡ አነገሠ ፡ አዋጁን ፡ በአዋጅ ፡ መለሰ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይትረኃዋ ፡ አብያተ፡ጣዖታት ፡ ይትዐጸዋ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አርዮስ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፡ ሦስት ፡ መቶ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰበሰቡ(የተሰበሰቡት ፡ ፪ሺ ፡ ፫፻፵፰ ፡ ናቸው ፡ ከእሊህ ፡ ፫፻፲፰ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ሆነው፡ ተገኝተዋል) ፡ አርዮስን ፡ አውግዘው ፡ ሃይማኖትን ፡ መልሰው ፡ (አቅንተው)፡ በሚለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ ለመጻሕፍቱ ፡ ሁሉ ፡ አርእስት ፡ ሰጥተዋል ። ብስራተ ፡ ማቴዎስ ፡ ሐዋርያ፡ ፩ ፡ እም ፡ ፲፪ቱ፡ ወ፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ብስራተ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፩፡ እም፡ ፸፡ ወ፪ቱ፡ አርድእት፡ ብስራተ፡ ሉቃስ፡ ወንጌላዊ፡ ፩ ፡ እም፸ወ፪ቱ፡ አርድእት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ብስራተ ፡ አብ ፡ ረድእ ፡ ትሩፍ ፡ ተናጋሪ ፡ በመለኮት ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ዘብዴዎስ ፡
ፍቁረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። መልእክተ ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክተ ፡ ጴጥ
ሮስ ። መልእክተ ፡ ዮሐንስ ። መልእክተ ፡ ያዕቆብ ። መልእክተ ፡ ይሁዳ ፡ መጽሐፈ ፡
ግብረ ፡ ልኡካን ፡ እያሉ ፡ (አርእስት ፡ ሰጥተዋል) ፡ የጸሐፊው ፡ ደግነት ፡ የታወቀ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጽሐፉ ፡ ደግነት ፡ ይታወቃልና ፡ ብለው ፡ (ጥቅ) ፡ ይደልዎ ፡ ለዘ
ያነብብ ፡ ቅድመ ፡ ይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለበዓለ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምዝ ፡ ያንብብ ፡
ወይምሀር ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወርቅ) ፡

ለአራት ፡ ለነገሥት ፡ ለግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ታሪክ ፡ የላቸውም ፡ እነሱ ፡ ለሌላው ፡ ታ
ሪክ ፡ ይሆናሉ ፡ እንጅ ።

መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ልኡካን ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዜና ፡ ሐዋርያት ፡ ንጹሐን ፡ እምጊዜ ፡
ዕርገቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

መጽሐፍ ፡ በያበላሉ ፡ ይፈታል ፡ ነገር ፡ ሹመት ፡ ዜና ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡
አብዝኖ ፡ መጻሕፍትኬ ፡ ያዘነግዕ፡ ልበ ፡ ይላል ። ሹመት ፡ ሲሆን ፡ ወነሣዕኩ ፡ መ
ጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ ይላል ። ዜና ፡ በቁሙ፡ መጽሐፍ ፡ ያለውን ፡ ዜና ፡ ልኡካን ፡ ያለ
ውን ፡ ሐዋርያት ፡ ብሎ ፡ አመጣ ። አንድም ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ልኡካን ፡ ዝው
እቱ ፡ ዜና ፡ ግብሮሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ንጹሐን ፡ ይላል ፡ መጽሐፍ ፡ ያለውን ፡ ዜና ፡
ግብር ፡ ያለውን ፡ ግብሮሙ ፡ ልኡካን ፡ ያለውን ፡ ሐዋርያት ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካረገ ፡ በኋላ ፡ ካረገ ፡ ዠምሮ ፡ ሐዋርያት ፡ ያስተ
ማሩትን ፡ ትምህርት ፡ ያደረጉትን ፡ ተአምራት ፡ የሠሩትን ፡ ትሩፋት ፡ የሚናገር ፡
መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ። አንድም ፡ ነቅዕ ፡ ንጹሕ ፡ ዘእምአንቅዕተ ፡ ሕግ ፡ ንጹሐን ፡
ይላል ፡ መጽሐፍ ፡ ነቁንም ፡ መንቂያውንም ፡ ነቅዕ ፡ ይላል ። ምስጢርን ፡ ከሚያ
ስገኙ ፡ ከሐዋርያት ፡ የተገኘ ፡ ምስጢር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ንጹሐንን ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡
ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ አልተናገሩትም ፡ አንትሙሰኬ ፡ ንጹሐን ፡ አንትሙ ፡ ካለ
ው ፡ ከወንጌል ፡ አምጥተው ፡ ተናግረውታል ፡ እንጂ ። መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡
ይላል ፡ አብነት ፡ ትርጓሜው ፡ አንድ ፡ ነው ፡

ዘጸሐፈ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡

የወንጌልን ፡ ነገር ፡ ያስተማረ ፡ ወንጌልን ፡ የጻፈ ፡ ሉቃስ ፡

ወፈነዎ ፡ ኀበ ፡ ታዎፊላ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ወንጌለ ።

ጽፎ ፡ ቀድሞ ፡ ወንጌልን ፡ ለጻፈለት ፡ ለታዖፊላ ፡ የሰደደው ፡ ሐዋርያት ፡ ያስተማሩ
ትን ፡ ትምህርት ፡ ያደረጉትን ፡ ተአምራት ፡ የሠሩትን ፡ ትሩፋት ፡ የሚናገር ፡
መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ፈነዎ ፡ መጠዎ ፡ ይላል ፡ መጠዎ ፡ ቢል ፡ ጽፎ ፡ ሲጨርስ ፡
ይመጣል ፡ ሰጥቶት ፡ መምህሩን ፡ ተከትሎ ፡ ይሄዳል ፡ ፈነዎ ፡ ቢል ፡ ዠምሮ ፡
ሳለ ፡ መምህሩ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይመጣል ፡ መምህሩን ፡ ተከትሎ ፡ ከሄደ ፡ በኋ
ላ ፡ ጨርሶ ፡ ሰዶለታል ።

www.ethiopianorthodox.org